# የሰብአዊ መብት ተሟጋቾች ድንጋጌ

ይህ ድንጋጌ የግለሰቦች፣ የቡድኖች እና የህብረተሰቡ አካል የሆኑ የተለያዩ ክፍሎች በአለም አቀፍ ደረጃ እውቅና የተሰጣቸውን ሰብአዊ መብቶች እና መሰረታዊ ነጻነቶችን ለማሳወቅ እና ለመጠበቅ ያላቸውን መብት እና ኃላፊነት ይደነግጋል።

09.12.1998

ድንጋጌው የጸደበት ቀን

ድንጋጌው በተባበሩት መንግስታት ጠቅላላ ጉባዔ በሙሉ ድምጽ ጸድቋል

## እነ ማን ናቸው የመብት ተሟጋች የሚባሉት?

ለሰብአዊ መብቶች መከበር የሚንቀሳቀስ ማንኛውም ወንድም ሆን ሴት፤ ማለትም ሃሳብን በመግለጽ ነጻነት፣ በሴቶች መብት፣ ወይም ህዳጣን ወይም የተመሳሳይ ጾታ ግንኙነት ያላቸው ወንዶች ወይም ሴቶች ወይም የጾአታ ለውጥ ያደረጉ ወይም የተለየ የጾአታ ግንኙነት ላላቸው ሰዎች መብት የሚታገሉ ሰዎችን ይጨምራል። እነዚህ ግለሰቦች በተናጠል ወይም ተደራጅተው ሊሆን ይችላል የሚንቀሳቀሱት።

## የሰብአዊ መብት ተሟጋቾችን እንዴት ነው ልትረዳቸው የምትችለው?

- ስለ ሰብአዊ መብት ተሟጋቾች ድንጋጌን መረጃዎችን ማሰራጨት
- የሰብአዊ መብት ተሟጋቾች የሚያከናውኗቸው ሥራዎቻቸው ተገቢውን እውቅና እንዲያገኙ አስተዋጽዖ ማበርከት
- ለሰብአዊ መብት ተሟጋቾችን እርዳታ እና ጥበቃ ለሚያደርጉ ድርጅቶችን ድጋፍ መስጠት
- አደጋ ላይ የተጋረጡ የመብት ተሟጋቾችን መደገፍ
- የመብት ተሟጋች ሁን! እያንዳንዱ ሰው መብት እና ኃላፊነትም አለበት

## ድንጋጌው ምን ያህል ቅቡልነት አግኝቷል?

ድንጋጌው ሰብአዊ መብቶችን ለማሳወቅ፣ ለመጠበቅ እና ለመከላከል፤ እንዲሁም ለሰብአዊ መብት ተሟጋቾች ጥበቃ ለማድረግ በሚጠቀሙ እጅግ ጠንካራና በአስገዳጅነታቸው በታወቁ አለም አቀፍ ሕጎች ላይ መሰረት ያደረገ ነው።

## ለሰብአዊ መብት ተሟጋቾች የተሰጡ መብቶች እና ጥበቃዎች

- በአገራቸው እና በአለም አቀፍ ደረጃ ሰብአዊ መብቶችን ማሳወቅ
- በተናጠል ወይም ከሌሎች ጋር በመሆን ለሰብአዊ መብቶች ጥብቅና መቆም
- ማህበራት እና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን የማቋቋም
- በሰላማዊ መንገድ የመገናኘት ወይም የመሰባሰብ
- ከሰብአዊ መብት ጋር የተያያዙ መረጃዎችን የመፈለግ፣ የመያዝ፣ የመቀበል እና የማቆየት
- ከሰብአዊ መብት ጋር የተያያዙ አዳዲስ ሃሳቦችን እና መርሆዎችን የማፍለቅ እና የመወያየት፤ እንዲሁም ተገባይነት እንዲያገኙ የማስተዋወቅ
- ለመንግሥት ባለሥልጣናት የሰሉ አስተያየቶችን የመስጠት እና አፈጻጸማቸውን እንዲያሻሽሉ ሃሳብ የማቅረብ፤ እንዲሁም በሰብአዊ መብቶች መረጋገጥ ላይ ስጋት የሚያሳድሩ ማናቸውም ነገሮች ሲፈጠሩ ቀድሞ የማሳሰብ
- በመንግስት ፖሊሲዎች እና አድራጎቶች ላይ ቅሬታዎችን የማቅረብ እና ለቅሬታዎቻቸው ምላሽ የማግኘት
- ሰብአዊ መብቶችን በመከላከል እረገድ ብቃት ያለው የሕግ ባለሙያ ድጋፍ የመስጠት ወይም ሌሎች የማማከር እና የድጋፍ አገልግሎቶችን መስጠት
- የፍርድ ቤት ግልጽ ችሎቶችን፣ የክስ ሂደቶችን እና የፍትህ ሂደቱን የመከታተል እና ከአገሪቱ ሕግ እና ከአለም አቀብ የሰብአዊ መብት ግዴታዎች ጋር በተስማማ መልኩ መፈጸሙን መገምገም
- ያለ ምንም ገደብ መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች እና በአባል አገራት ከተቋቋሙ ድርጅቶች ጋር ግንኙነት የማድረግ
- በበቂ ሁኔታ ፍትህ የማግኘት
- የሰብአዊ መብት ተሟጋችነት ሥራቸውን ወይም ሙያቸውን በሕጋዊ መንገድ የማካሔድ
- የሰብአዊ መብት ጥሰቶችን በሰላማዊ መንገድ ለመቃወም እንዲችሉ አስተማማኝ ጥበቃ የሚያደርፍ የአገር ውስጥ የሕግ ማዕቀፍ መኖር
- ሰበአዊ መብቶችን ለማስከበር የሚረዱ ግብዓቶችን የማፈላለግ፣ የመቀበል እና የመጠቀም

አንቀጽ 1, 5, 6, 7, 8, 9, 11, 12 and 13

## የመንግስታት ኃላፊነት

- ሰብአዊ መብቶችን የመጠበቅ፣ የማሳወቅ እና በተግባር የመፈጸም
- በግዛቱ ውስጥ ያሉ ሰዎች ሁሉ ሰብአዊ መብቶች እና መሰረታዊ ነጻነቶቻቸውን ሙሉ በሙሉ የተቀዳጁ መሆኑን ማረጋገጥ
- አስተማማኝ በሆነ መልኩ መብቶች እና ነጻነቶች እንዲረጋገጡ የሚያስችሉ ሕጎችን፣ አስተዳደራዊ እና ሌሎች እርምጃዎችን መውሰድ
- የሰብአዊ መብት ጥሰት ሰለባ የሆኑ ሰዎች ትክክለኛ ፍትህ የሚያገኙበትን መንገድ ማመቻቸት
- የሰብአዊ መብት ጥሰት በተፈጸመ ጊዜ አፋጣኝ እና ገለልተኛ የሆነ ምርመራ እንዲካሄ ማደረግ
- እያንዳንዱ ሰው በሰብአዊ መብት ዙሪያ በሚያከናውናቸው ሥራዎቹ ሳቢያ ሊደርስበት ከሚችሉ ማናቸውም አይነት የመብት ጥሰት፣ ማስፈራሪያ፣ የወታደራዊ ጥቃት፣ ያልተገባ መድልዎ፣ ጫና ወይም ማንኛውም አይነት የዘፈቀደ ድርጊት እንዳይፈጸምበት አስፈላጊ የሆነውን እርምጃ ሁሉ መውሰድ
- በሲቪል፣ ፖለቲካል፣ ኢኮኖሚክ፣ ማህበራዊ እና ባህላዊ መብቶች ዙሪያ በኅብረተሰቡ ዘንድ ግንዛቤ መፍጠር
- ብሄራዊ የሰብአዊ መብት ተቋም እንዲመሰረት ማድረግ እና እንዲስፋፋም ድጋፍ መስጠት
- የሰብአዊ መብቶች ትምህርት በሁሉም ደረጃ ለሚገኙ መደበኛ ትምህርት እና በባለሙያዎች ስልጠናም ላይ እንዲሰጥ ማበረታታት እና ማመቻቸት አለበት።

አንቀጽ 2, 9, 12, 14 and 15

## የእያንዳንዱ ሰው ኃላፊነት

- ሰብአዊ መብቶችን ማሳወቅ፣ ዲሞክራሲን መጠበቅ እና ተቋማቱም የሰውን መብት እንዳይጥሱ ማረጋገጥ
- የሌሎችን ሰዎች ሰብአዊ መብት ለመጣስ በሚያመቹ የሙያ ዘርፎች ላይ የሚሰሩ ሰዎች በተለይም፤ ፖሊስ፣ ባለሥልጣናት፣ ጠበቃዎች፣ ዳኞች፣ ወዘተ መብትን በመጠበቅ ረገድ ኃላፊነት ያለባቸው መሆኑ

አንቀጽ 10, 11 and 18



Design by Oh ! Ilaliss